Ethiopian Sport & Culture Federation in Europe
በአውሮፓ የኢትዮጵያውያን የስፖርትና ባህል ፌዴሬሽን

# ዋሊያ ቀይ ቀበሮና ሉሲዎች በርቱ ተበራቱ፤




እግር ኳስ በሀገራችን ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ በ1924 ዓ/ም አዲስ አበባ ውስጥ ይኖሩ በነበሩ የውጭ ሀገር ተወላጆች (ፈረንጆች ) የተጀመረ ሲሆን ምንም እንኳን በአለም አቀፍ ደረጃ በመዝገብ ሠፍሮ ባይገኝም በ1935 ዓ/ም አዲስ አበባ ላይ ከጅቡቲ ጋር ግጥሚያ ተደርጎ እንደነበረ ‘History of Ethiopian Soccer’ በሚል የተጻፈ ታሪክ ያስረዳል ፡፡

በ1943 መጀመሪያ አካባቢ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን በህግና ደንብ ተመስርቶ የክለቦች ውድድር የተጀመረበት ወቅት ሲሆን ፤ እ.ኤ.አ በ1950 ለመጀመሪያ ጊዜ የሲውድን ብሄራዊ የእግር ኳስ ቡድን የወዳጅነት ግጥሚያ ለማድርግ ወደ ሀገራችን የገባ የመጀመሪያ የውጭ ሀገር ብሄራዊ ቡድን ነበር፡፡በተመሳሳይም ጊዜ በ1952 ለመጀመሪያ ጊዜ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን ለእግር ኳስ ጨዋታና ለጉብኝት ወደ አውሮፓ የተጓዘበት ወቅት ነበር፡፡




እ.ኤ.አ በ1957 ሶስት ሀገሮች ኢትዮጵያ፤ግብፅና፤ሱዳን፤ የአፍሪካን ዋንጫ ካርቱም ላይ መስርተው ሱዳን ሀገሯ ላይ ስታስቀር 2ተኛውን በ1960 ግብፅ ሀገሯ ላይ አዘጋጅታ ስታስቀር በ 1962 ኢትዮጵያ የሶስተኛው የአፍሪካ ዋንጫ ሀገሯ ላይ አዘጋጅታ የዋንጫ ባለቤት እንደነበረች Soccer ያስረዳል፡፡

በመቀጠል ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ በ1968 ለ6ተኛው የአፍሪካ ዋንጫ ኢትዮጵያ ላይ ተዘጋጅቶ ኢትዮጵያና ኮንጎ ለዋንጫ ፍፃሜ ቀርበው ኢትዮጵያ በኮንጎ ተሸንፋ ዋንጫ ያጣችበትና በጣም በብዙ ሺህ የሚገመት የአዲስ አበባ ነዋሪ የተበሳጨበት ጊዜ ነበር ፡፡ በመቀጠልም የ10ኛው የአፍሪካ ዋንጫ በሀገራችን ተደርጎ እንደነበረና ውጤት አልባ ሆነናል፡፡

ብሄራዊ ቡድናችን በ1974 በነመንግስቱ ወርቁ አሰልጣኝነትና በነንጉሴ ገብሬ ኮከብ ተጫዋችነት በሊቢያ ቤንጋዚ ላይ የተደረገውን የ13 ኛውን የአፍሪካ ዋንጫ ለመጀመሪያ ግዜ ማጣሪያውን አልፎ የተሳተፈበት ግዜ እንደነበረና እነሆ አሁን ከ31 ዓመት በኋላ ለአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ በማለፏ ከኢትዮጵያ አልፎ በአውሮፓ በአሜሪካና በአውስትራሊያ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን ከመጠን በላይ አስደስቷል ፡፡




በሀገራችን ኢትዮጵያ ለእግር ኳስ ጨዋታ ከፍተኛ ፍቅር የመኖሩን ያህል ስፖርቱ በምንም አይነት ሁኔታ ሊያድግ አለመቻሉንና ነገር ግን በተለይ በአሁን ሰዓት ብሄራዊ ቡድናችን ያሳደረው ከፍተኛ መነቃቃት ጥሩ ቢሆንም ለመጪው የአፍሪካ ዋንጫ ተካፋይ የመሆን ተስፋ ፈንጥቋል፡፡ በተለይ ቀይ ቀበሮ የሚል ስያሜ በመያዝ ጥሩ ውጤት እያስመዘገበ ያለው የታዳጊ ብሄራዊ ቡድንና በተመሳሳይና በተደጋጋሚ ለአፍሪካ ዋንጫ አልፈው ውጤት እያስመዘገቡ ያሉት የሴቶች ብሄራዊ ቡድናችን(ሉሲዎች ) መልካም አርያነታቸውን እያሳዩ ይገኛሉ፡፡

በዚህ አጋጣሚ የአውሮፓ ስፖርትና ባህል ፌዴሬሽን ሀገራችንን ኢትዮጵያን እያስጠሩ ላሉት ብሄራዊ ቡድኖቻችን ከፍተኛ አድናቆቱንና ምስጋናውን ይገልጻል፡፡

የአውሮፓ ስፖርትና ባህል ፌዴሬሽን ከተመሰረተ 10ኛ አመቱን ያስቆጠረ ሲሆን ፤ፌዴሬሽኑ በየአመቱ በተለያዩ የአውሮፓ ከተሞች የእግር ኳስ ውድድር እያዘጋጀ አያሌ ተጫዋቾችንና ስፖርት አፍቃሪዎችን እያሰባሰበ የሚገኝ ሲሆን በተለይ አንዳንድ ወጣቶች በአውሮፓ ውስጥ በታዋቂ ክለቦች ውስጥ ተቀጥረው የሚጫወቱ ሲሆን እነኝህን ወጣቶች የኢትዮጵያ እግርኳስ ፌዴሬሽን ሊጎበኛቸው እንደሚገባ ሳንጠቁም አናልፍም፡፡




በ1970ዎቹ አካባቢ አዲስ አበባ ውስጥ ለተለያዩ ክለቦች በመጫወት ከዚያም ለወጣት ቡድን፤ ለተስፋውና ለዋናው ብሄራዊ ቡድን እንዲሁም ለሸዋና ለሃረርጌ ምርጥ ቡድን ይጫወት የነበረና በአሁን ሰዓት ኑሮውን በአውሮፓ ያደረገው አቶ ከበደ ሀይሌ ሲሆን ፤የታዳጊ፤የሴቶችና የብሄራዊ ቡድናችን የእግር ኳስ ውጤት ከልብ እንዳስደሰተው ይናገራል ፤ብሄራዊ ቡድናችን ከ31 ዓመት በኋላ ወደ አፍሪካ ዋንጫ መምጣት ደስታዬ ወሰን የለውም ይላል፡፡ በተለይ ትዝ ይለኛል ያኔ ጃፓን በምታዘጋጀው የአለም የወጣቶች የእግር ኳስ ውድድር ላይ ተካፋይ ለመሆን ከምድባችን ካለፍን በኋላ የመጨረሻውን ማጣሪያ ከሌላ ምድብ አልፎ ከመጣው ከአልጄሪያ ጋር አዲስ አበባ ላይ ባዶ ለባዶ በመሆን ሀገራቸው ላይ በአደረግነው የመልስ ጨዋታ 1-0 በሆነ ውጤት ተሸንፈን ወደ ጃፓን ባለመሄዳችንና ባለመሳተፋችን ለረጅም ግዜ ቁጭት ነበረብኝ፤ግን አሁን ብሄራዊ ቡድናችን ባስመዘገቡት ውጤት ረክቻለሁ ይላል፡፡

በመቀጠልም በድሮው የመኩሪያና የምድጦር ቡድን ተጫዋች የነበረው በኋላም የመጀመሪያው የሸዋ ምርጥ ተሰላፊ አቶ ግርማ ሳህሌ በብሄራዊ ቡድኖቻችን ውጤት ደስታውን የገለፀ ሲሆን በተለይ በኛ ዘመን የነበሩ ተጫዋቾች በአካል ብቃትም ሆነ በኳስ ቴክኒክ አሉ ከሚባሉ የአፍሪካ ቡድኖች የማይተናነስ እንደነበረ ይናገራል ለ10ኛው አፍሪካ ዋንጫ ከተመረጥን በኋላ ለልምምድና ለወዳጅነት ጨዋታ ጀርመንና ቻይና እንደተጓዝን አስታውሳለሁ በዛ ግዜ ከፍተኛ የሆነ የእግር የኳስ ፉክክር የታየበት ግዜ በመሆኑ ለብሄራዊ ቡድን ለመመረጥ ልክ ከጎጆ ቤት ላይ አንድ ሳር

እንደመምዘዝ ይቆጠር ነበር፡፡ከ31ዓመት በኋላ ለአፍሪካ ዋንጫ ከማለፍ ባሻገር ለቀጣዩ ትውልድ አርያ መሆናቸው አስደስቶኛል፡፡

የእግር ኳስ ፌዴሬሽኑ ብዙ ስራ ይጠብቀዋል ይለናል፡፡ ለዚህ ጉዳይ ትኩረት በመስጠት በቅርቡ የእግር ኳስ ፌዴሬሽኑ የሚመለከታቸውን ባለሙያዎችና ታዋቂ ስፖርተኞችን በመጋበዝ ጉባዔ አዘጋጅቶ እንደነበር የሚታወቅ ሲሆን በተለይ መንግስትን በማስጨነቅና በግንባር በመነጋገር በየቀበሌው በትምህርት ቤቶችና በተለያዩ ቦታዎች የመዝናኛ ስፍራዎችን በማመቻቸት ባጠቃላይ እግር ኳሱ የሚዳብርበትና ብሎም ንቁ ዜጋ የምናፈራበት መድረክ ይሆናል እንላለን፡፡ በዚህ በምንኖርበት አህጉር መንግስት 8 እና 9 ቤቶችን ከመስራቱ በፊት በመጀመሪያ የአካባቢው ነዋሪ የሚዝናናበትን ስፍራ ሲያመቻቹ ይታያል፡፡ ለዚህም ጤናማና ብርቱ ትውልድ ለማፍራት መሰረት ይሆናል ብለን እናምናለን ፡፡

ፌዴሬሽኑ በየአመቱ በሚዘጋጀው የእግር ኳስ ውድድር ላይ የቀድሞ ታዋቂ የነበሩ ስፖርተኞችን በክብር እንግድነት የሚጋብዝ ሲሆን ከተጋበዙት እንግዶች ውስጥ የጅምናስቲክ አባት አቶ ግርማ ቸሩ፤የ3ተኛው፤ የ6ተኛው፤የአፍሪካ ባለውለታዎች አቶ መንግስቱ ወርቁና አቶ ሊቻኖ ቫሳሎ ፤ የ10ኛውና የ13ተኛው የአፍሪካ ዋንጫ ተሰላፊ አቶ ንጉሴ ገብሬ ፤እንዲሁም ለ10ኛው ለ13ኛው ዋንጫ ተሰላፊ የነበሩት አቶ አለማየሁ ሀ/ስላሴ(ፊኛ) ስለሀገራችን የስፖርት እድገት ከሰጡት የተለያየ አስተያየት ቀንጨብ በማድረግ ለናንተ ለስፖርት ታዳሚዎች ጀባ ብለናል፡፡

ከታች የሚታየውን ሊንክ በመጫን የቪዲዮውን መልእክት ይከታተሉ፡፡

http://www.youtube.com/watch?v=48lENQQPOLQ (Prepared by Dagne Mekonnen) ፡፡ **በተለይ** ከአሁን በፊት ለ7ኛ ግዜ የአፍሪካ ሻምፒዮና የነበረችው የግብፅ ብሄራዊ ቡድንና የ4 ግዜ ሻምፒዮና የነበረችው የካሜሩን ብሄራዊ ቡድን በዘንድሮው በደቡብ አፍሪካ በሚካሄደው የ29ኛው የአፍሪካ ዋንጫ ላይ ተሳታፊ ሳይሆኑ ቀርተዋል፡፡ኬፕፌርዲያ ለአፍሪካ ዋንጫ የመጀመሪያ ተካፋይ ስትሆን የአፍሪካ እግርኳስ መስራች ኢትዮጵያ ከ31 ዓመት በኋላ ብቅ ብላለች፡፡

**16 ሀገሮች በአራት ምድብ ተከፍለው የሚጫወቱ ሲሆን ኢትዮጵያ ከባድ ምድብ ገጥሟታል፡፡**

| ምድብ አንድ ፤ | ምድብ ሁለት፤ | ምድብ ሶስት፤ | ምድብ አራት፤ |
|---|---|---|---|
| ደቡብ አፍሪካ | ጋና | ዛምቢያ | ኮትዲቯር |
| **ኬፕፌርድ** | **ዴሞክራቲክ ኮንጎ** | **ኢትዮጵያ** | **ቶጎ** |
| **ሞሮኮ** | **ኒጀር** | **ቡርኪናፋሶ** | **አልጀሪያ** |
| **አንጎላ** | **ማሊ** | **ናይጀሪያ** | **ቱኒዚያ** |

ከሁለት አመት በፊት የአለም ዋንጫን ያስተናገደችው ደቡብ አፍሪካ  የዘንድሮውን ውድድሩ በተመቻቸ ሁኔታ ለማስተናገድ አምስት ስታዲየሞችን የመረጠች  ሲሆን ይህም ከጃንዋሪ 19 ቀን እስከ ፌብርዋሪ 10  2013 እንደሚጠናቀቅ ታውቋል፡፡

በዚህ አጋጣሚ መልካም ውጤት ለብሄራዊ  ቡድናችን እንመኛለን፡፡ ግዜ ሲያገኙ www.escfe.org ይጎብኙልን ፡፡





**ESCFE:** Post bus 56924, 1040AX AMSTERDAM, The Netherlands KvK (registration nr.): Amsterdam, 3432528
Tele: **0031206892205 / www.escfe.org / www.escfe.net.** **Bank COMMERZ BANK AG, Kontonumber: 3303062, BLZ: 500 400 00, IBAN: - DE43 5004 0000 0330 3062 00.**